## ስለቀጣዩ ትግል ለህብረቱ አመራር ለውይይት የቀረበ

# በህዝባዊ አጀንዳ ለህዝባዊ ትግል
# ተአማኒ አመራር

በግንቦት 97 ምርጫ ህዝባችን አንደኛ በነቂስ ወጥቶ ተሳትፎ በማድረጉ፤ ሁለተኛ የወያ/ኢህአዴግን መሪዎች በምንም አይነት በማያወላዳ ሁኔታ በዝረራ በማሸነፉ፤ ሶስተኛ ደግሞ ይህንን ድሌን በጠራራ ፀሃይ አልነጠቅም ብሎ ከነዚህ ጥቂቶች ጋር እልህ በተጋባ መልክ ትንንቅ በመያያዙ በፖለቲካ ያገባናል ለሚሉ ሃይሎች በማስተላለፍ ላይ ያለው መልእክት ለማንኛችንም ምንም ምርጫ የተወ አይመስልም።

ለኢህአዴግ መሪዎች ያቀረበው ምርጫ ሽንፈትን በፀጋ ተቀብሎ በቀረበላቸው የብሄራዊ እርቅ ሃሳብ መስማማት ወይም ደግሞ በለየለት ሽብር በመሰማራት አገር ለመግዛት መሞከር የሚል ምርጫ ነው። ይህንን ሁለተኛውን አካሄድ ከመረጡ ተጨማሪ ዴሞክራሲ ቀርቶ ከእንግዲህ አስራ አምስት አመት ሲመፃደቁበት የቆዩበትን የይስሙላ ዴሞክራሲ ፍንጭ እንኳን ለማረጋገጥ የሚችሉበት ሁኔታ ውስጥ አይሆኑም። ድሮውንም ቢሆን ሳይደላደል በአንድ እግሩ ቆሞ የነበረው ነፃ ፕሬስ ዛሬ ያለበትን ሁኔታ ስንመለከት፤ ከሰኔ ወዲህ ያለአንዳች ተጠያቂነት የፈሰሰውን ደምና የተፈፀመውን ግፍ ስናይና በአጠቃላይ በሰብአዊ መብቶች ጉዳይ ዛሬ ሃገሪቱ የዘቀጠችበትን ደረጃ ስንታዘብ በዚህ ምርጫቸው የተነሳ የኢህአዴግ መሪዎች ሃገራችንን፤ ህዝባችንንና ራሳቸውንም ወደ ጥፋት ይዘው እየነጎዱ መሆናቸው ግልፅ ይመስለናል።

በትግል ላይ ያለው የኢትዮጵያ ህዝብ ለሃገራችን ዴሞክራሲያዊ ሃይሎችም ያቀረበላቸው አማራጭ የዚያኑ ያህል ግልፅ ነው። የመጀመሪያው አማራጭ ህዝቡ አጀንዳየ ብሎ የሚንቀሳቀስበትን የድምፄ ይከበር አጀንዳ ሳይሸራርፉ መቀበል፤ የትግሉ ባለቤት እኔ ነኝ ብሎ ራሱ በማካሄድ ላይ ያለውን ትግል በጥቂቶች መደራደር/መመሳጠር እንተካ ብለው ሳይግደረደሩ ከህዝቡ ትግል መደባለቅ፤ በዚህ ተጋድሎው ከሚከፍለው መስዋእትነት የሚመጥን ፍሬ እንዲያገኝ ጥራት፤ ተአማኒነትና ተጨባጭነት ያለው አመራር ሰጥቶ ለድል ማብቃት የሚል ነው። ከዚህ ውጭ ያለው አማራጭ የዴሞክራታይዜሽኑን ሂደት መቀልበስ አሜን ብሎ ተቀብሎ፤ ለሽብር አገዛዝ ተንበርክኮ፤ ህዝብን አውላላ ሜዳ ላይ በትኖና አጋፍጦ ከታሪክ መድረክ ተዋርዶ መውረድ የሚል አማራጭ ብቻ ነው። ይህ አማራጭ የህዝባችን የዴሞክራታይዜሽን ተጋድሎ ምናልባት ለአንድ ትውልድ የሚተላለፍበት ዘግናኝ ሁኔታ እንዲሰፍን የሚያደርግ አካሄድ በመሆኑ ህብረታችን እንኳን ሊመርጠው ቀርቶ ሊያስበውም ይቀፈዋል።

በዚህ ወይ ከህዝባዊ ድል ወይ ደግሞ ከሽብርተኛ አገዛዝ ሌላ መፈናፈኛ በማይሰጥ ሁኔታ ውስጥ እያለን በተቃዋሚው ሰፈር ዴሞክራሲን ቀስ በቀስ ለመገንባት፤ ሰላምንና መረጋጋትን ለማስፈን በሚል ሰበብ የህዝቡን የድምፄ ይከበር አጀንዳ እስከ ቀጣዩ ምርጫ ለአምስት አመት በይደር ለማስቀመጥና የህዝቡን የትግል መአበል በጥቂቶች "የሰከነ" ግርግር ለመተካት የሚንቀሳቀሱ ወገኖች እንዳሉ እናያለን። ከአምናው ዘንድሮ የመብት መራቆት በሰፈነበትና መሰረታዊ የተባሉ ዴሞክራሲያዊ እሴቶች ደብዛቸው ጠፍቶ የሽብር አገዛዝ በተተከለበት ሁኔታ በቅድሚያ በህዝብ ድልና በኢህአዴግ መሪዎች ሽንፈት ዴሞክራሲ የሚገነባበት መሰረት እስካልተጣለ ድረስ ስለ "ዴሞክራሲ ግንባታ" ማውራት በህዝብ ትግል ማሾፍ ነው ብለን ስለምናምን ይህንን አካሄድ ባለን አቅም ሁሉ መታገልና ማጋለጥ ይገባናል።

በኛ በኩል የኢህአዴግ የሽብር ጎዳና ለማንም አይጠቅምም ብለን በማመንና ይህንን የጥፋት ጉዞ ለመግታት ከተደራጀ ህዝባዊ ትግልና ከድል በመለስ ምንም ተስፋ የለም ከሚለው ፅኑ እምነት በመነሳት የምናስተጋባው ጥሪ በጣም ግልፅ ነው። ተቃዋሚ ነን፤ የህዝብ ወገኖች ነን ትግሉ ይቀጥል የምንል ከሆነ የህዝቡን አጀንዳ በከፊል ሳይሆን በሙሉ ማንገብ ይኖርብናል። የህዝቡን አጀንዳ እንግብናል ካልን ደግሞ ከሽብርተኛው አገዛዝ በድርድር ምንም አይጠበቅም ብለን በህዝባዊ ትግል ጎዳና መሰማራት ይኖርብናል። በህዝባዊ ትግል ጎዳና እንሰማራ ካልን ደግሞ ትግሉ ተአማኒ

ነት፤ ተጨባጭነትና ጥራት ያለው አመራር እንደሚያስፈልገው ተገንዝበን ለዚህ ራሳችንን ብቁ ለማድረግ መንቀሳቀስ አለብን።

## 1. ትግሉን እንቀጥል ካልን.....ህዝባዊ አጀንዳ

አጀንዳችን አፈናን እየተቃወመና እየተቋቋመ እዛው በዛው ደግሞ ትግሉ በህዝባዊ ድል እልባት የሚያገኝበትን የድምፅ መከበር ስትራቴጂያዊ ጥያቄ ያነገበ ጥንድ አጀንዳ መሆን ይኖርበታል። ሁለቱ የሚተጋገዙ እንጂ የሚነጣጠሉ አይደሉም።

የህዝባዊው አጀንዳ መጀመሪያ ገፅታው መሰረታዊ መብቶች ዙሪያ መንቀሳቀስ የሚል ነው። ይህ አጀንዳ "በግፍ የታሰሩ ዜጎች ይፈቱ" "የነፃው ፕሬስ ባልደረቦች ከእስር ተፈትተው ያለአንዳች ጫናና ተፅእኖ የህዝብ ድምፅ መሆናቸውን ይቀጥሉ" በሚሉ መደበኛ ሊባሉ በሚችሉ ዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎች የሚወሰን አይደለም። ከነዚህ እኩል "ዝቅተኛና" መሰረታዊ ብለን በምንገምታቸው " የኢህአዴግ መንግስት ያሰራቸውን በይፋ አሰርኩ ይበል! ሊስታቸውን ያውጣ! የታጎሩበትን ቦታ ለቤተዘመድ ያስታውቅ!፤ የጅምላ መቃብሮች ተከፍተው ዜጎች በስነስርአት ይቀበሩ፤ ተጠያቂነት ይኑር፤ ከግንቦት ጀምሮ ስለተፈፀመው ግፍ አለም አቀፍ አጣሪ ኮሚሽን ይቋቋም" በሚሉት ለህዝባችን አንገብጋቢ ለወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች ደግሞ የማይዋጡም የማይተፉም ጥያቄዎች ዙሪያ ተንቀሳቅሰን ህዝባችንን ማንቀሳቀስ ይኖርብናል።

በነዚህ መሰረታዊ ጥያቄዎች ዙሪያ ትግልን ከቀጠልን በህዝብ ትግል የምንጎናፀፉት ማንኛዋም ድል በአንድ በኩል ለህዝቡ ወገኖች የድል በጎ አዙሪት በሌላ በኩል ደግሞ ለወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች የማፈግፈግና የሽንፈት አስከፊ አዙሪት እምርታ ስለምትፈጥር "ትንሽ" ተብላ የምትናቅበት ሁኔታ የለም። እርግ-ጥ በነዚህ ነጥቦች ዙሪያ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች በአሻፈረኝነት ሊቀጥሉ ይችላሉ። ያኔ ደግሞ ህዝባዊው ትግል የሚካሄደው ከእለት እለት ከዝቅተኛም ዝቅተኛ እየሆኑ በሚመጡ የመብት፤ የዴሞክራሲና ከነጭራሹ የህልውና ጥያቄዎች ዙሪያ ስለሚሆን የኢህአዴግ መሪዎች በዚያው ልክ ከእለት እለት ይበልጥ እያየለና እየተቆጣ የሚሄድ ህዝባዊ የትግል ማእበል እየተነሳባቸው፤ ከእለት እለት የፖሊሱ፤ የሰራዊቱና የአባሎቻቸው ልብ ይበልጥ እየተከፈለባቸው፤ ከእለት እለት አለም አቀፉ ኮሙኒቲ ይበልጥ እየተጠየፋቸውና እያወገዛቸው የማይወጡት የውድቀት አዙሪት ውስጥ የሚገቡበት ሁኔታ ይፈጠራል።

የህዝባዊው አጀንዳችን ሁለተኛ ገፅታ የህዝቡ ድምፅ ይከበር የሚለው ጥያቄ ነው። በአሁኑ ወቅት አልፎ አልፎ እንደሚታየው ይህ መሰረታዊ የህዝብ የትግል አጀንዳ "ለጊዜው" ወደ ጎን ተትቶ መሰረታዊ መብቶች ይከበሩ፤ የታሰሩት ይፈቱ በሚሉት መፈክሮች ብቻ አተኩሮ የመታገል አዝማሚያ አለ። የማገሪቱ ዴሞክራቶች በሙሉ በነዚህ የመብት ጥያቄዎች ላይ አተኩረው መታገላቸው ተገቢ ነው ብንልም ለዚህ አላማ ቁልፍ ቦታ ሰጥቶ የሚካሄደው ትግል ለአንዲት ሰከንድም ቢሆን የህዝብ ድምፅ ይከበር የሚለውን መፈክራችንን ሊያስረሳን አይገባም እንላለን። ከእንግዲህ ከወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች የሚነጠቅ ማንኛውም ድል የሚገኘው በነዚህ ጥያቄዎች ዙሪያ ትግሉ እያየለ ከቀጠለና የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች ለማፈግፈግ ከተገደዱ ብቻ ነው። እዚህ የትግል ደረጃ ከተደረሰ ደግሞ ከፍ ብለን የጠቆምነው በህዝባዊው ሰፈር የበጎ በእነሱ ሰፈር ደግሞ የሽንፈት አዙሪት ተንቀሳቅሱዋል ማለት ነው። የህዝባችን ትግል እንዲህ አይነቱን እምርታ መቀስቀስ የሚችልበት ደረጃ ከደረሰ ደግሞ የህዝብ ድምፅ ይከበር በሚለው አጀንዳ ተገፍቶ ዴሞክራሲያዊ ስርአት እስኪሰፍን ድረስ ትግሉ ሳያቋርጥ መቀጠሉ የግድ ነው።

ይህ ካልሆነ የኢህአዴግ መሪዎች የተፈጠረውን በጎ እምርታ ወይም ዳይናሚክስ ለመስበር የሚያስችላቸው ፋታ የምንሰጥተበት አደገኛ ክፍተት ይከሰታል። ይህ ክፍተት ከተፈጠረ ደግሞ ፀረ ህዝቦቹ በትግል ከእጃቸው የተፈለቀቀውን ድል ሁሉ ጊዜና አጋጣሚ ጠብቀው መልሰው ሊቀሙን የሚችሉበት፤ በትግል የተፈቱት እስረኞቻችን በሌሎች የሚተኩበት ወይም ደግሞ በትግል የተመለሱት መሰረታዊ መብቶቻችን ተመልሰው የሚነጠቁበት ሁኔታ ይከሰትና ነገሩ ሁሉ ታጥቦ ጭቃ ይሆናል ማለት ነው።

## 2. ህዝባዊ አጀንዳ ካልን .....ህዝባዊ ትግል1.

ህዝባችን ድምፁንም ለማስከበር አጀንዳውን አንግቦ በመንቀሳቀስ ላይ በመሆኑ የህዝብ ወገኖች ነን የምን
ልም ይህንን አጀንዳ አንግበን እንደባለቀው ካልን የትግሉ ባለቤት ራሱ ህዝባችን እንደሆነ መቀበላችን የግድ  ስለሆነ የ
ሚካሄደውን ትግል ህዝባዊ ገፅታ በምንም አይነት ሌላ የትግል ስልት መተካት አይቻልም። ትጥቁን ይፍታና እኛ በአለ
ም አቀፉ ኮሙኒቲ እገዛ ተደራድረን ነፃ ፕሬሱንም እናስመልሳለን፤ የፖለቲካ እስረኞችም እናስፈታለን፤ የዳኝነት ነፃነ
ት የሚረጋገጥበትም ሁኔታ እናመቻቻለን፤ ከነ ጭራሹ በቅርቡ ዶ/ር በየነ ጴጥሮስ ለሪፖርተር ጋዜጣ በሰጠው ቃለ ም
ልልስ እንደጠቀመው "በሃገራችን በፖለቲካ ምክንያት ሰው የማይታሰርበትን ሁኔታ" ለማመቻቸት ከኢህአዴግ መሪዎ
ች ጋር እንደራደራለን ማለት እየታገለና እየተሰዋ ጣፊያ ለተነሳ ህዝብ ድርድር በሚሉ ፈሊጥ ጥቂቶች ከጥቂቶች ጋር
በሚመሳጠሩበት ሂደት ታናሽና ታላቅ ይሰደድልሃል እንደማለት ያህል አጓጉል አካሄድ ነው።

ይህ አባባላችን ለሃቀኛ ድርድር መቆም እንጂ ድርድርን መቃወም ማለት አይደለም። ሃቀኛ ድርድር ደ
ግሞ የማይታለፉ ቅድመ ሁኔታዎች አሉት። አንደኛ ደጋግመን እንዳልነው ማንኛውም ድርድር የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛ
ዝ በህዝብ ትግል ተገዶ የሚገባበትና ህብረተሰቡ በተጠንቀቅ ቆሞ የሚያጅበው ሂደት መሆን ይኖርበታል። ሁለተኛ የ
ዚህ ድርድር አጀንዳ በግልፅ የህዝቡ ድምፅ ይከበር የሚለውን ነጥብ መጨመር ይኖርበታል። ሶስተኛ ፍሬያማ እንዲ
ሆን ከተፈለገ የሁሉም የፖለቲካ ሃይሎች፤ የሲቪኩ ማህበረሰብ ተወካዮች፤ የገበሬዎች፤ የሰራተኞች፤ የነጋዴዎች፤ የ
ሴቶች፤ የወጣቶችና እንዲሁም የሌሎች የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ተወካዮች በሚሳተፉበት ሁሉን አቀፍ አገራዊ
መድረክ አማካኝነት መሆን ይኖርበታል። ይህንን ሁሉ እውን ለማድረግ የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች በቅድሚያ ከተያያ
ዙት የሸብር ጎዳና በህዝብ ትግል እንዲያፈገፍጉ መደረግ ይኖርባቸዋል።

## 3. ህዝባዊ ትግል ካልን.....ህዝባዊ አመራር

ከግንቦት ወር ጀምሮ ያለውን ህዝባዊ ትግል ሁኔታ ስንመለከት አንድ ቁም ነገር እንታዘባለን። ሚያዝያ 3
0 ቀን 1997 በቅንጅት ከተጠራው ሰላማዊ ሰልፍ ወዲህ ህዝባችንን (ከጥሩምባ መንፋቱና ከሶስቱ ቀን የስራ ማቆም አድ
ማ በስተቀር)  ሰላማዊ ሰልፍ ወጥቶም ሆነ በሌላ ሰላማዊ ዘዴ ተቃውሞውን እንዲያሰማ በተቃዋሚ ድርጅቶች በኩል
በይፋ የተጠየቀበት ጊዜ የለም። ሆኖም ባለፉት ዘጠኝ ወራት የህዝብ ቁጣና የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች ትንኮሳ እየተጋ
ገዙ የቀሰቀሱዋቸውና ብዙ መስዋእትነት የተከፈለባቸው ሰላማዊ ሰልፎች፤ ስራ ማቆም አድማዎችና ሌሎች ግብታዊ ተ
ጋድሎዎች ተካሂደዋል። ትግሉ ከእንዲህ አይነቱ ግብታዊነት ወጥቶ የፖለቲካ አመራርና ቅንብር የሚያገኝበት ዘዴ ካ
ልተበጀ ሃገራችንን የሚጠብቃት ችግርና አደጋ ግልፅ ነው። አንደኛ ፍሬው የማይታይ መስዋእትነት መስላቸት ሊጋብዝ
ይችላል። ሁለተኛ ትግሉ ያልተደራጀና ያልተጋገዘ ትግል ሆኖ እስከ ቀጠለ ድረስ ይዋል ይደር እንጂ የተደራጀው የወ
ያኔ/ኢህአዴግ ሃይል ሊያከሽፈው ይችላል። ከዚህ አጣብቂኝ ለመውጣት ከተፈለገ ለዚህ ህዝባዊ ተጋድሎ ህዝባዊ አ
መራር መስጠት ያስፈልጋል ስንል በመሰረቱ ሁለት ነገሮችን ለመጠቆም ነው።

አንደኛ በያለበት ክፍ ብለን የጠቀስናቸውን የመሰረታዊ መብቶች ጥያቄ እያነሳ ተራ በተራና በግብታዊነ
ት የሚንቀሳቀሰው ትግል በአንድነት እንዲካሄድ አመራር መስጠት ያስፈልጋል። ሁለተኛ አመራር መስጠት ስንል በዚ
ህ መልክ በአንድነት ለምንቀሰቅሳቸው የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ከነዚህ መሰረታዊና አጣዳፊ መፈክሮች አልፎ
የሚሄድና ለትግሉ ስኬታማ እልባት ብለን የምንጨብጠውንና የምንታገልለትን የህዝብ ድምፅ ይከበር መፈክር ለማስ
ጨበጥ መስራት ይኖርብናል ማለታችን ነው።

ከነዚህ ጥንድ የአመራር ትግባራት አንፃር ያሉብን ችግሮች ግልፅ ናቸው። ደግመን ደጋግመን "የትግል
አንድነት ጥሪ" እያልን ብዙ መግለጫዎች አውጥተናል። ነገር ግን እስካሁን እንደሚታየው የተለያዩ የህብረተሰቡ ክፍ
ሎች በጋራ ሊነሱ ቀርቶ ተማሪውንና ወጣቱን በሃገርም ሆነ በአዲስ አበባ ደረጃ በአንድ ቀንና በአንድ መፈክር ከዳር እ

ስከዳር በአንድ ላይ እንዲነሳ ማድረግ እንኳን አልቻልንም። ይህ የሚያሳየን አንድ ቁም ነገር ነው። አመራር መስጠት ማለት ጥሪ ከመወርወር አልፎ በነዚህ የተሰበጣጠሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ በተቀነባበረና በተደራጀ መልክ ተሰማርተው እነዚህ ክፍሎች በአንድነት እንዲነሱ ጥንቃቄ በተመላበት ሁኔታ ድርጅታዊ ስራ የሚሰሩ ጥቂትም ቢሆኑ የተዋቀሩ ዜጎች ያስፈልጋሉ ማለት ነው።

በስትራቴጂያዊ መፈክራችንም አንፃር በተለይ ዛሬ የህዝቡ ድምፅ ይከበር የሚለውን ጥያቄ በድርጅት ደረጃና በፅናት ያነገበው አንድ ህብረታችን ብቻ ሆኖ በዚህ በኩል ያለው ትግል "ባለቤት ያጣ" በሚመስልበት ሁኔታ መፈክሩን በመግለጫና ውሳኔዎች አማካኝነት ወርውሮ መተው አይቻልም። ይህንኑ ጥያቄ አንስቶ በትግል ላይ ላለው ህዝባችን ተአማኒነት ያለው አቅጣጫ ለማስጨበጥና በዲፕሎማሲውም መስክ ትግላችን የጭፍን ተቃውሞ ትግል ብቻ እንዳይመስልብን በድምፅ መከበርና በድርድር ጉዳይ ያሉንን ተጨባጭ የመፍትሄ ሃሳቦች በማኒፌስቶ መልክ አዘጋጅተን በሰፊው መበተን ይኖርብናል።

ለዚህ አይነቱ የህዝባዊ አመራር ሃላፊነት ብቁ ሆኖ ለመገኘት ከፈለግን ደግሞ ይህ ጥረታችን ተአማኒነትና ተጨባጭነትን እንዲኖረው ለማድረግ መንቀሳቀስ ይኖርብናል።

ተአማኒነት ያለው አመራር መገንባት የሚለው ጉዳይ አንገብጋቢ ሆኖ የሚቀርብበት ምክንያት ዛሬ በአለው ሁኔታ መሰረታዊ መብቶችን ለማስከበርና ድምፅ ይከበር በሚለው ጥንድ አጀንዳ ህዝቡ ለሚያካሂደው ትግል የተደራጀ አቅጣጫ የሚሰጥ አመራር መጥፋቱ ነው። የህብረቱ የቀድሞ መሪዎች "የሰከነ ፓርላሜንታዊ ተቃውሞ" በሚል ሰበብ እጅ ከሰጡ ወዲህ የህዝቡ ድምፅ ይከበር የመሰለን ከባድ አላማ ቀርቶ መሰረታዊ የህዝብ መብቶች ይከበሩ ለሚለው አጣዳፊ የህልውና ጥያቄ እንኳን ህዝባዊ ትግሉን መቀስቀስም ሆነ መምራት የሚችሉበት ሁኔታ ውስጥ አይደሉም። የቅንጅቱ ችግር አመራሩ እንዳለ ታፍሶ እስር ቤት መግባቱና ተተኪ አመራር አለመፍለቁ ብቻ አይደለም። የድምፅ ይከበርን ጥያቄ በይፋ አራግፎታል። የድርጅቱ መሪዎች ፓርላማ ለመግባት ካቀረቡዋቸው ስምንት ቅድመ ሁኔታዎች በአለም አቀፍ ኮሙኒቲው አጋፋሪነት ከኢህአዴግ ጋር ተደራድረው በተለይ በፓርላማ የአሰራር ደንብ ጉዳይ ያቀረቡት ቅድመ ሁኔታ ተቀባይነት ካገኘ በድርጅት ደረጃ ወስነው በሙሉ ወይም አሁን እንደተያዘው እየተንጠባጠቡ ፓርላማ መግባታቸው ይህንን አመራር ክፍተት የሚያባብስ እንጂ የሚደፍን አካሄድ አይሆንም።

እንደ ድርጅት ሁለቱን የህዝብ አጀንዳዎች አጣምሮ የያዘ ግልፅ ህዝባዊ አቋም ያለው አንድ ሃይል ህብረታችን ብቻ ቢሆንም አመራሩ በውጭ በመገኘቱ ብቻ ከሃገራችን ዴሞክራቶችም ሆነ ከአለም አቀፉ ኮሙኒቲ አንፃር ከባድ የሆነ የተአማኒነት ችግር እንዳለበት ሁላችንም የምንገነዘበው ነው። ታሪክ ለጣለብን አገራዊ አደራ ብቁ ሆነን ለመገኘት ከፈለግን የመጀመሪያ መጀመሪያ ተግባራችን "ውጭና ውስጥ" የሚለው ክፍፍል ለማክሸፍ ተንቀሳቅሰን ተአማኒነታችንን መገንባት ይሆናል።

ዛሬ በተቃዋሚው ጎራ (በተለይ ደግሞ በህብረታችን ውስጥ የተፈጠረውና ነገ ደግሞ በቅንጅቱ ውስጥ የማይቀረው ክፍፍል አንዳንዶች ለማሳመን እንደሚፈልጉት በውጭ ባሉና በውስጥ ባሉ ዴሞክራቶች መሃከል ያለ ክፍፍል እንዳልሆነና ያለው ልዩነት በአመዛኝ መልኩ የሚንፀባረቀው *እዛው አገር ቤት ውስጥ* እንደሆነ ለማስጨበጥ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል። በፓርላሜንታዊ ትግል ከተሰማሩት ጥቂቶች አንፃር የግንቦትን ድሉች ለማስከበር የሚደረገው ህዝባዊ ትግል ተቀጣጥሎና ተቀነባብሮ ይቀጥል የሚሉ እዛው አገር ቤት ውስጥ ሰፍር ቁጥር የሌላቸው ዴሞክራቶችና አገር ወዳድ ሃይሎች አሉ። ቀውሱ የህብረቱ የቀድሞ መሪዎች በአጠቃላይ የህዝቡን ፍላጎት በተለይም ደግሞ በሃገር ውስጥ ያሉ አባላትን፤ በምርጫ ተወዳድረው በጭብርብር ተሸንፋችሁዋል የተባሉትን ተወዳዳሪዎቻችንንና መራጩን ህዝብ፤ የሃገር ሽማግሌችን፤ በየድርጅቱ ስር የተካተቱ የሴቶች፤ የወጣቶች፤ የገበሬዎች ተወካዮችን ሃሳብ በመቃረን ፓርላማ ለመግባት ወስነው ትግሉን አመራር አልባ በማድረጋቸው የተከሰተ ቀውስ ነው። በአለው የአፈና ሁኔታ በጥንቃቄ ለመራመድ ብቻ ሲባልና ከእሳት እራትነት ራስን ጠብቆ ትግልን በወጉ ለመምራት ባላቸው ጉጉትና ሃላፊነት ብቻ በመመራት ለጊዜው እዩን እዩን ባይሉም ቅሉ በነዚህ ድርጅቶች ውስጥ ያሉ ብዙሃን የተወሰደውን እርምጃ እንደሚቃወሙና ህዝባዊ ትግሉን ከወጣቱና በአጠቃላይ ከህዝቡ ጎን ሆነው እንደዚሁም በውጭ ካሉ የድርጅቶቻቸው አባላትና ከህብረቱ አመራር እየመከሩ ለመቀጠል ቁርጠኛነት እንዳላቸው ከብዙ አቅጣጫዎች የሚደርሱን ጥቆማዎች ያረጋግጡልናል። በ

መሆኑም ይ-ህንን ሃቅ ለሚመለከተው ሁሉ ለማስጨበጥ በፖለቲካውና በዲፕሎማሲው መስክ እየታገልን በተጨባጭ ደግሞ እዛው ሃገር ውስጥ ይህንን የአመራር ክፍተት ለመሙላት መንቀሳቀስ ይኖርብናል። ይህ ማለት ደግሞ ለህዝብ አጀንዳ በህዝብ ትግል የሚሉት በውስጥም በውጭም ያሉ ሃይሎች ተፈላልገው፤ ተገናኝተውና ተቀነባብረው የሚሰሩበት ሁኔታ መመቻቸት ያስፈልጋል ማለት ስለሆነ ህብረታችን እዛው አገር ቤት የህቡእ መዋቅሩን ዘርግቶ በዚህ አማካኝነት በተለያዩ በትግል ላይ ባሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ መንቀሳቀስ መጀመሩ ይደር የማይባል አንገብጋቢ ተግባር ሆኖ ይቀርባል ማለት ነው።

በአንገብነው ምንም የማይወጣለት ህዝባዊ አቋም ላይ በሃገር ውስጥ የህቡእ መዋቅር ዘርግተን "ዲያስፖራና የውስጥ ታጋዮች" የሚለውን ፕሮፓጋንዳ ከሰበርን ዛሬ በሃገራችን ያለውን የተአማኒ አመራር ክፍተት እንደፍናለን። ይህንን ተአማኒነት ለማጎልበት ደግሞ የህቡእ መዋቅር ከመዘርጋቱ ጋር ተያይዞ እዛው ሃገር ቤት ውስጥ ህዝባዊ አቋማችንን የሚያስተጋባ ከራሱ ከስሙ ጀምሮ የትግል ስትራቴጂያችንን የሚያንፀባርቅ "የግንቦት ድምፅ" የተሰኘ የህቡእ ጋዘጣ መጀመሩ ሌላ የማይታለፍ ተግባር ይመስለናል። ይህ ለጊዜው በተወሰኑ ቀራጥ ዜጎች አማካኝነት የምንዘረጋው መዋቅርና የምንጀምረው ጋዜጣ ጉዳይ መስመር ከያዘ ዛሬ በሃገር ውስጥ ከተያዘው ትግልም ሆነ ከዘላቂው የፖለቲካ ግባችን አንፃር ይህ ነው የማይባል ጥቅም ይኖረዋል።

በአንድ በኩል እስከዛሬ ስናስተጋባው የቆየነውና ከፍ ብለን እንደጠቀስነው ምንም ፍሬ ያልሰጠው የትግል አንድነት ጥሪ በአየር ላይ ተወርውሮ የሚቀር አይሆንም። ተማሪው፤ ነጋዴው፤ ዴሞክራቱ፤ ወላጆች….በአንድነት በአንድ ቀን በአንድ ጥያቄ ይነሱ ብለን የምናስተጋባውን ጥሪ በተማሪው፤ በነጋዴው፤ በዴሞክራቱ፤ በወላጆች…. ውስጥ ተተክለው ድርጅታዊ ስራ በሚሰሩ ታጋዮቻችን አማካኝነት ተግባራዊ የምናደርግበት ሁኔታ አመቻቸን ማለት ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ህዝባዊ ብለን ከልብ የምናምንበትን መስመራችንን ለማስፋፋት ከሌሎች የፖለቲካ ሃይሎች ተለይተን (አንዳንዴም የነዚህን ሃይሎች መስመር ተቃውመን) የምንለው፤ የምንፅፈው፤ የምንተቸው ሁሉ እንደ አሁኑ "የጥቂት ስደተኞች አጉል ልፈፋ" ተብሎ መጣጣሉ ያከትምና በሃገራችን ዴሞክራቶችና አገር ወዳዶች ዘንድ ይበልጥ ተአማኒነትና ተደማጭነት የሚያገኝበት በአጭሩ ለፖለቲካ ትግሉ ጥራት ያለው አመራር የምንሰጥበት ሁኔታ ይመቻቻል ማለት ነው።

ነ.ጎ.
07/03/06